EthioLion
KIAB
KINIJIT INTERNATIONAL ADVISORY BOARD ■ ቅንጅት ዓለም አቀፍ አማካሪ ቦረድ
1629 K Street, NW, Suite 300, Washington, DC 20006
Tel (202) 973-0170, Fax (202) 3313759

September 3, 2008

# "ረሃብ የፖለቲካ ነፃነት ዕጦት ውጤት ነው!"

ዛሬ በጨካኝና በአንባገነኑ ወያኔ ሥር የምትገኘው ውድ አገራችን ውስጥ እንደዜጋ ለመኖር የምንችለው ያለምንም አማራጭ የተሰጠነንና እንድንገዛበት የወጣልንን አምባገነን ሕግ አክብረን ስንገኝ ብቻ በመሆኑ በምንመካባትና በምንኮራባት አገራችን በተዋራጅነትና በድህነት አሮንቃ ውስጥ እንድንኖር ተገደናል:: የዳቦ ቅርጫት የተባለችው አገራችን ኢትዮጵያ አጥፊ ዕቅድና ተንኮል እየተዘረጋባት ሕዝቡ መንደሩና ቀዬው የገሃነብ እሳት እንዲሆንበት በመደረጉ የሞተው እየሞተ የቻለው እየተሰደደ ያልቻለው ደግሞ በመከራ ውስጥ ፍዳውን በማየት ላይ ይገኛል::

ኢትዮጵያ የወደቀባትን ርኃብና የኑሮ ውድነት እሽክርክሪት መነሻ ለማብራራት በርካታ ዝርዝር መረጃዎችን ማቅረብ በተቻለ ነበር:: ሆኖም ሕዝባችንን እየጨረሰ ያለው የፖለቲካ ሰራሽ ርሃብ ዝም ብሎ በአንድ ሰሞን የመጣ ችግር ሳይሆን መነሻና መድረሸው አንድና አንድ ነው:: ይህም "የፖለቲካ ነፃነት አለመኖር" ወይም "የአስተዳደሩ ሥርዓት በጥቂት አንባገነኖች መያዝ" ሲሆን መንስኤነቱ አሁን ለተከሰተው ርሃብ ብቻ ሳይሆን የበርካታ ችግሮቻችን መሰረት ነው:: ለምሳሌ የሕዝቡን ዕድገት ተብትበው እንዳይዙ ከተዘረጉት መዋቅሮች ውስጥ የኢኮኖሚ ድቀትን የሚወልዱ የገበያ ስርዓቶች፥ ትውልድን የሚያዘቅጥ የትምህርተ ፖሊሲ፥ዘረኝነትና ሙሰኝነት ወዘተ መጥቀስ ይቻላል::

በአገራችን ኢትዮጵያ ከምንጊዜውም በበለጠ የኑሮ ውድነት፥ ሥራ አጥነትና የዋጋ ግሽበት ሰማይ በመድረሳቸው ለዕለት ተዕለት ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮች እንደ ውሃ መብራት ነዳጅና ምግብ የመሳሰሉት ባለፈው ዓመት ብቻ ከ330% በላይ ዋጋቸው ያደገበት ወቅት ሆኗል:: በደረሰው ርሃብ ሳቢያ የተከሰተው የምግብ እጥረት በሽታ ሕፃናቱን እየጭረሰ በመሆኑ ቁጥራቸው ከፍተኛውን የእልቂት ሥፍራ እንዲይዝ

አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም በቀላሉ ሊድኑ የሚችሉ በሽታዎች ሕክምና ባለመገኘቱ ሳቢያ በምግብ እጦት የተዳከመውን ሕዝብ በማጣደፍ ላይ ናቸው፡፡

በተከታታይ ባሳለፍናቸው የአገዛዝ ሥርዓቶችና አሁንም ጭምር የተሸከምናቸው ችግሮችና ውድቀቶች ርሃቡም ቢሆን ሊፈታ ሚችለው ሕዝቡ የራሱን መሪዎች በምርጫ ሲያገኝ ብቻ በመሆኑ የሰላማዊ ትግሉን ማጠናከር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር ለመፍታት ቀደም ሲል የጀመርነውን ትግል በመቀጠል በሠላማዊ መንገድ በመታገል በሕዝቡ መሃል ገብቶ የነበረው በኢ/ር ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቅንጅት ከብዙ ውጣ ውረድና ውስብስብ ችግር በኋላ ትግሉን በአዲስ መልክ ተያይዞታል፡፡ ስለዚህ በቀን አንድ ብር እንኳን ገቢ የሌለው ወገናችን  አንድ በቆሎ በሶስት ብር በሚቀርብበት የገብያ ንረት ውስጥ የሚገኝ ስለሆነ ከዚህ በሃቀኛ ተቃዋሚነትና ለሕዝብ ከቆመው ድርጅት ጋር በመወገን አገራችንን ከወደቀችበት አዘቅት ለማውጣት እንድትሰለፉ አደራችን የጠበቀ ነው፡፡

## አስቸኳይ ጥሪ

ከላይ ከብዙ በጥቂቱ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከ6-7 ሚሊዬን የሚሆን የአገራችን ሕዝብ ዛሬም እንደገና በረሃብ ላይ እንደሚገኝ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ምንም እንኳ ትግላችን የፖለቲካ ቢሆንም ይህ በአገራችን ሕዝብ ላይ የደረሰው ርሃብ አጣዳፊና አስቸኳይ በመሆኑ ረሃብ ጊዜ የማይሰጥ የቀን ጅብ ነውና ወገንን ለማዳን በሚደረገው ርብርብ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳያግደን በአገር ውስጥና በውጭ አገር የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፥ ዓምአቀፍ የሰብዓዊ ዕርዳታ ድርጅቶች፥ የሐይማኖትና የፖለቲካ ተቋማት ወዘተ ትኩረታችሁን ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ እንድትለግሱ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

**ቅንጅት ዓለምአቀፍ አማካሪ ቦርድ**

EthioLion.Com